የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6[th] Year No. 39
ADDIS ABABA - 27[th] June, 2000

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፱ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
ስለ ቅርስ ጥናትና አጠባበቅ የወጣ
አዋጅ ...................................................... ገጽ ፩ሺ፫፻፵፭

CONTENTS

Proclamation No. 209/2000
Research and Conservation of Cultural Heritage
Proclamation ........................................... Page 1345

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፱/፲፱፻፺፪

## ስለቅርስ ጥናትና አጠባበቅ የወጣ አዋጅ

ቅርስ የአንድ ሕዝብ የዘመናት የኑሮ እንቅስቃሴ ፡ የሥራ እና የፈጠራ ክንውን መዘክር ስለሆነ ፤

ስለሰው ፡ ስለሌላውም ምድራዊ ሕይወት ዝርያ አመጣጥ ፡ እንዲሁም ስለተንዛዘበት የለውጥና የእድገት ሂደት በማጤን ተፈጥሮንና አካባቢን ይበልጥ ለመረዳት ለሚደረግ ጥናትና ምርምር ቅርሶች ምትክ የሌላቸው የመረጃ ምንጮች ስለሆኑ ፤

ቅርስ ለሳይንስ እድገትና እንዲሁም በጠቅላላ የሰውን ዘር በሚመለከት እውቀት ላይ ያለው ድርሻ የጎላና ዓለም አቀፋዊ ስለሆነ ፤

ኢትዮጵያ የየራሳቸው ታሪክና ባህል ያላቸው ብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚገኙባት ፡ ሕዝቦቿም ባሳለፉት የረጅም ዘመን ታሪክ በዓለም የባህል ቅርስነት የተመዘገቡትን ጨምሮ የበርካታ ቅርሶች ባለቤት ለመሆን የቻሉ ስለሆኑ ፤

ተተኪው ትውልድ ስለ ማንነቱ መገለጫ ለሆነው ታሪኩና ባህሉ ጥልቅና ሰፊ ግንዛቤ ይበልጥ እንዲኖር ቅርስ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወት ቅርስን መንከባከብና መጠበቅ የእያንዳንዱ ዜጋ ፡ የኅብረተሰቡና የመንግሥት ግዴታ በመሆኑ ፤

ለቅርስ የሚያስፈልገው እንክብካቤና ጥበቃ የሚሟላበትን መንገድ መቀየስ እና በነዚሁ ላይ በማናቸውም ደረጃ የሚደረግ የጥናትና የምርምር ሥራ ሥርዓት በያዘና የሀገሪቱንና የዜጎቿን መብትና ጥቅም በሚያስጠብቅ መልክ እንዲከናወን ማድረግ ስለሚገባ ፤

## PROCLAMATION NO. 209/2000

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR RESEARCH AND CONSERVATION OF CULTURAL HERITAGE

WHEREAS, Cultural Heritage constitutes the imprints of a people's age-old way of life, labour and creativity;

WHEREAS, Cultural Heritage constitutes an indispensable source of information for the purpose of study and research regarding the origin and evolution of man and other forms of life and thereby for the better understanding of nature and environment.

WHEREAS, Cultural Heritage makes a major and universal contribution to the development of science and regarding the whole gamut of human knowledge generally;

WHEREAS, Ethiopia, a country of nations, nationalities and peoples with history and culture of their own, has through the course of its long history acquire numerous cultural heritage including those which have been registered in the World Cultural Heritage List;

WHEREAS, Cultural Heritage plays a major role in enabling the next generation to acquire profound and extensive awareness about its culture and history, which is the expression of its identity, and hence the protection and preservation of cultural heritage has been made the responsibility of each citizen, the society and the statse;

WHEREAS, it has become necessary to devise ways and means for the full protection and preservation of cultural heritage and to ensure that the research of Cultural Heritage at all stages is carried out in a way consonant with the national interest and the rights of the people;

ያንዱ ዋጋ 4·40
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

ሀ) የብራና ጽሁፍ ፡ የድንጋይ ላይ ጽሁፎችና ሥዕሎች፡ የድንጋይ መሳሪያዎች ፡ ከወርቅ ፡ ከብር፡ ከነሐስ ወይም ከብረት ወይም ከመዳብ ከሌሎች ንጥረ ነገሮች ከእንጨት ፡ ከድንጋይ ፡ ከቆዳ ፡ ከዝሆን ጥርስ ፡ ከቀንድ ፡ ከአጥንትና ከአፈር ወይም ከሌሎች ነገሮች የተሰሩ ቅርጾችና ምስሎች እንዲሁም የአርኪዎሎጂና የፓሊዮንቶሎጂ ቅሪቶች ፡

ለ) ጽሁፍና የግራፊክ ዶክመንት ወይም የሲኒማቶግ ራፊና የፎቶግራፍ ዶክመንት ፡ የድምጽ ወይም የቪዲዮ ቅጅ ዶክመንት ፡

ሐ) ከወርቅ ፡ ከብር ፡ ከነሐስ ፡ ከመዳብ ወይም ከሌሎች ነገሮች የተሰራ ገንዘብ ፡

መ) የብሔር ፡ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መገልገያ ጌጥ ወይም ባህላዊ ዕቃ ።

፱· "የቅርስ ምዝገባ" ማለት ቅርስን ለመለየት ፡ ለመቆጣጠር፡ ለማጥናት ለመንከባከብና ለመጠገን ፡ ለትምህርትና ለመዝናኛነት አገልግሎት የሚውሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲቻል ስለ ቅርሱ ሰፊ መረጃ ለማሰባሰብ በተዘጋጀ ቅጽ መመዝገብና እንደ አመቺነቱ በፎቶግራፍ፡ በፊልምና በቪዲዮ መቅረጽንም ይጨምራል ።

፲· "ጥገና" ማለት ጥንታዊ ይዘቱ ሳይለወጥ ለቅርሶች የሚደረግ አጠቃላይ እንክብካቤና ጥበቃ ነው ።

፲፩· "ቁፋሮ" ማለት ማንኛውም ከምድር በታች የሚገኝን ቅርስ ለማውጣትና ለማጥናት በሰው ኃይል ወይም በመሳሪያ መቆፈር ነው ።

፲፪· "ሙዚየም" ማለት ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ያልሆነ ቅርሶችን የሚሰበስብ ፡ የሚጠብቅና የሚጠግን ፡ ለምርምር ለጥናት ፡ ለማስተማሪያና ለመዝናኛነት ስብስቦችን በሚገባ አዘጋጅቶ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው ።

፲፫· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ።

፬· ዓላማ

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል ፡

፩· ቅርሶች በታሪክ ምስክርነታቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ሳይንሳዊ ምዝገባና ቁጥጥር ማከናወን ፡

፪· ቅርሶችን ከሰው ሰራሽና ከተፈጥሮ አደጋዎች መከላከል፡

፫· ከቅርሶች የሚገኙ ጥቅሞች ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ልማቶች እገዛ እንዲያደርጉ ማስቻል እና

፬· ቅርሶችን ማግኘትና ማጥናት ።

፭· ዋና መሥሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን በማናቸውም ቦታ ለማቋቋም ይችላል ።

፮· የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡

፩· አግባብ ካለው አካል ጋር በመተባበር ቅርሶችን ይመዘግባል ፡

፪· ቅርሶችን ይንከባከባል ይቆጣጠራል ፡ እንዲሁም ስለቅርሶች መረጃ ይሰበስባል ፡ ቅርስ መሆን ያለመሆኑን ይለያል ፡ ደረጃም ያወጣል ፡

፫· ስለቅርስ ምንነት ፡ ጥቅምና አጠባበቅ ፡ አስፈላጊውን ትምህርትና ምክር ይሰጣል ፡



(a) parchment manuscripts, stone paintings and implements, sculptures and statues made of gold, silver, bronze, iron, copper or of any other mineral or wood, stone, inscriptions of skin, ivory, horn, archaeological and bone or earth or of any other material, and also Palaeontological remains;

(b) written and graphic documents or cinematographic and photographic documents or sound and video recordings;

(c) coins made of gold, silver, bronze, copper or of any other materials;

(d) ethnographic implement, ornament or any other cultural object of nations, nationalities and peoples.

9) "Cultural Heritage Registration" means registration in the form prepared to collect wide information of Cultural Heritage, which shall include photographing, recording in film or video, as appropriate, so as to put in place the means to catalogue, inspect, study, protect and conserve cultural heritage and facilitate utilization of same for the purpose of recreation and education;

10) "Conservation" means a general protection and preservation activity carried on a Cultural Heritage without changing its antique content;

11) "Excavation" means the activity of systematic digging up any Cultural Heritage situated underground with manpower or machine in order to conduct a study on such Cultural Heritage;

12) "Museum" means a non-profitable organization which collects, preserves and repairs Cultural Heritage renders service to the public by preparing and organizing collections for their use in research, study, education and entertainment.

13) "Person" means a physical or juridical person.

4. *Objectives*

The Authority shall have the following objectives:

1) carry out a scientific registration and supervision of Cultural Heritage so that, Cultural Heritage, as bearing witnesses to history, may be handed down from generation to generation;
2) protect Cultural Heritage against man-made and natural disasters;
3) enable the benefits of Cultural Heritage assist in the economic and social development of the country; and
4) discover and study Cultural Heritage.

5. *Head Office*

The Authority shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

6. Powers and Duties of the Authority

The Authority shall have the following powers and duties:

1) registers Cultural Heritage in cooperation with the appropriate body;
2) protects and supervises Cultural Heritage; collects information on Cultural Heritage, define the nature and classify the standards of same.
3) give the necessary education and advice on the content, benefit and preservation of Cultural Heritage;

ለ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፲፱/፩/፣ ፳፩፣ ፳፪/፪/፣ ወይም ፴፭ ድንጋጌ የተላለፈ እንደሆነ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እስራት ወይም እስከ ብር ፫ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

ሐ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፳፬ ፣ አንቀጽ ፳፯ ወይም አንቀጽ ፴(፩) ፣ ፵፪(፩) ወይም ፵፫(፪) ድንጋጌ የተላለፈ እንደሆነ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ወይም ከብር አሥር ሺ እስከ ብር አሥራ አምስት ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፪· በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከበድ ያለ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው፣

ሀ) በቅርስ ላይ የስርቆት ወንጀል ከፈፀመ ከሰባት ዓመት በማያንስ ከአስር ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

ለ) ሆን ብሎ በቅርስ ላይ የማፍረስ ወይም ጉዳት የማድረስ ወንጀል ከፈፀመ ከአስር ዓመት በማያንስ ከሃያ ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፣

ሐ) በሥራ ኃላፊነታቸው አጋጣሚ ያገኘውን ቅርስ የሚሰርቅ ወይም የሚያሰርቅ ወይም ጉዳት እንዲደርስ የሚያደርግ ከአስራ አምስት ዓመት በማያንስ ከሃያ ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፵፮· ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደንብ የማውጣት ሥልጣን አለው።

፪· ሚኒስትሩ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አለው።

፵፯· የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

፩· የቅርሶች ጥናትና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር ፴፮/፲፱፻፹፩ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪· ማንኛውም ሕግ ወይም የተለምዶ አሠራር ሁሉ ይህን አዋጅ የሚቃረን ከሆነ ይህን አዋጅ በሚመለከት ጉዳይ ተፈፃሚነት አይኖረውም ።

፵፰· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ፣ ሰኔ ፳ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



(b) violates the provisions of Articles 19(1), 21, 22(2) or 35 of this proclamation shall be punished with imprisonment of not exceeding one year or with fine not exceeding Birr 3000 or with both;

(c) violates Articles 24 or 27 or 30(1) 42(1)or 43(2) of this proclamation shall be punished with rigorous imprisonment from three to five years or with fine from Birr 10,000 to 15,000 or with both.

2) Unless the Penal Code provides for a more severe penalty, any person who:

a) commits theft on Cultural Heritage shall be punished with rigorous imprisonment of not less than seven years and not exceeding ten years;

(b) destroys or damages Cultural Heritage intentionally shall be punished with rigorous imprisonment not less than ten years and not exceeding twenty years;

(c) in the exercise of his official duty destroys, or damages or abstracts Cultural Heritage or causes them to be abstracted, in order to obtain an unlawful enrichment shall be punished with rigorous imprisonment of not less than fifteen years and not exceeding twenty years.

46. *Power to Issue Regulations and Directives*

1) The Council of Ministers has the power to issue Regulations for the implementation of this proclamation.

2) The Minister shall have the power to issue directives for the implementation of this proclamation.

47. *Repealed and Inapplicable laws*

1) Study and Protection of Cultural Heritage proclamation No. 36/1989 is hereby repealed.

2) Any law or practice shall, in so far as it is inconsistent with the provisions of this proclamation, have no force or effect in relation to matters provided for in this proclamation.

48. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 27th day of June, 2000.

Done at Addis Ababa this 27th day of June, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE